# የፊሊጵስዩስ ጥናት(1)

## ለፊሊጵስዩስ ጥናት ቅድመ ዝግጅት

በሐዋ ሥራ 16፥9-10 ባለው ክፍል እንደምናነበው ጳውሎስ በራዕይ ወደ መቄዶንያ እንዲሄድ በተደረገበት ጥሪ ጀምሮ፥ በጳውሎስና በሲላስ ታስሮ በመገረፍ፥ በእስር ቤቱ ጠባቂ መዳንና በልድያ መገኘት ምክንያት የተነሳ ነው ይህች ለወንጌል አስገራሚ ድጋፍ በማድረግ የታወቀችው የፊሊጵስዩስ ቤተ ክርስትያን የተመሰረተችው።

በ2ኛ ቆሮ 8፥1-4 ባለው ክፍል እንደምንመለከተው ይህች ቤተ ክርስትያን ለመስጠት የቻለችው ባለጠጋ ቤ/ክርስትያን ስለሆነች ወይም በውስጧ ባለጠጎች ስለበዙባት ሳይሆን ልባቸው በትክክለኛው ሥፍራ ስለነበረ እንደሆነ ከዚህ ክፍል እናስተውላለን።

የፊሊጵስዩስ መልዕክት ምንም እንኳን በመጠኗ አነስተኛ ሆና ብትታይም በአማኝ ህይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛና ጠቃሚ እውነቶች በተለያዩ መንገዶች የምታንጸባርቅልን እንደሆነች በቀላሉ ማየት እንችላለን። ከእነዚህም መሃል ሁለቱ ብቻ ማየት እንሞክራለን። የመጀመሪያው ክርስቶስ ለአማኝ ምኑ ነው የሚለው ላይ በማተኮር፤

- ምዕራፍ አንድ ክርስቶስ ለአማኝ ህይወት ነው በሚለው ሃሳብ ላይ ያተኩራል።
- ምዕራፍ ሁለት ክርስቶስ ለአማኝ የትህትና ምሳሌ በሚለው ሃሳብ ላይ ያተኩራል።
- ምዕራፍ ሶስት ክርስቶስ ለአማኝ ዓላማ(ግብ) እንደሆነ ሲያስገነዝበን፤
- ምዕራፍ አራት ደግሞ ክርስቶስ ለአማኝ ሃይሉ (ብርታቱ) እንደሆነ ያሳየናል።

ሌላው የፊሊጵስዩስን መልዕክት ልናይ የምንችልበት መንገድ ደግሞ ደስታ የሚለውን ሃሳብ በመመርኮዝ ይሆናል። ሐዋርያው ከእስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው አራት መልዕክቶቹ ውስጥ የፊሊጵስዩስ መልዕክት አንደኛው ነው። ምንም እንኳን መልዕክቱ ከእስር ቤት ይጻፍ እንጂ በውስጡ የሚያስተላልፈው ሃሳብ ከእስር ቤት የተጻፈ መሆኑን እስከሚያጠራጥር ድረስ በደስታ መልዕክቶች የተሞላ ነው። በአራቱ ምዕራፎች ውስጥ ብቻ ደስታ የሚለውን ሃሳብ አስራ ስድስት ጊዜ ያህል እናገኛለን።

- በምዕራፍ አንድ በመከራ ውስጥ ሊኖረን ስለሚችለው ደስታ
- ሁለተኛው ምዕራፍ ሌሎችን በማገልገል ስለሚገኘው ደስታ
- ሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ክርስቶስን በማወቅ ስለሚገኘው ደስታ
- አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ በመስጠት ስለሚገኘው ደስታ ያስተምሩናል።

# ጥናት አንድ (የሐዋ ሥራ 16፡6-34)

የጥናቱ ዓላማ፡- እግዚአብሄር በሰዎች ህይወት መልካም ሥራውን እንዴት እንደሚጀምርና እንዴትም ደግሞ በታማኝነት ከፍጻሜ እንደሚያደርስ በአንድነት ለመማር፡፡

የጥናት መክፈቻ፡- እግዚአብሄርን እየፈለከው እንደነበርክ ሆኖ ታስባለህ ወይ?

1. ሐዋ ሥራ 16፥6-34 በማንበብ ከጳውሎስ ጋራ ከሚጓዙት አንዱ አድርገህ ራስህን ብትቆጥር የእግዚአብሄርን ፈቃድ እየታዘዝክ እንደሆነ የሚያረጋግጥልህ ሁኔታ ምንድነው?
2. ከቁጥር 6 እስከ 12 ባለው ክፍል እነዚህን የወንጌል ሰባኪዎች እግዚአብሄር ወደዚህ ሥፍራ ስለመራበት አመራር ምን ታያለህ?
3. በቁጥር 13-15 እነጳውሎስን እግዚአብሄር የመጀመሪያዋ አማኝ ወደሆነችው ወደ ልድያ ይመቸዋል። ወደዚህች ሴት የተመሩበትንና አስቀድመው ወደ መቄዶንያ የተመሩበትን ሁለቱን አነፃጽር።
4. እነኚህ የተመለከትካቸው የአመራር ሁኔታዎች እግዚአብሄር አንተን ሊናገርህና ሊመራህ ስለሚችልበት መንገድ ምን ትማራለህ?
5. የባሪያይቱ ልጅ ባለቤቶች እግዚአብሄርን ሲሰራ እንዳያዩት የከለከላቸው ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ? (ቁ 19-21) አንተስ እግዚአብሄርን ሲሰራ እንዳታየው የሚከለክሉህ የራስህ የሆኑ አመለካከቶችና አጀንዳዎች እንዳሉ ታስባለህ?
6. በቁ 22-24 ውስጥ ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ሊሰማቸው ይችላል ብለህ የምታስባቸውን ስሜቶችና በውስጣቸው ሊሰሙ የሚችሉአቸውን ድምፆች ተናገር።
7. ጳውሎስና ሲላስን በዚህ ዓይነት መከራና ስደት ውስጥ እንዲዘምሩ ያስቻላቸው ነገር ምን ይመስልሃል? (ቁ 25)
8. የእስር ቤቱን ጠባቂ ወደራሱ ለመመለስ እግዚአብሄር የተጠቀመባቸው ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው?
9. በልድያ፥ በወህኒ ጠባቂውና ምናልባትም በሚርተኛይቱ ልጅ ሕይወት እግዚአብሄር ሥራውን በመጀመር የፊሊጵስዩስን ቤ/ክ ሲመሰርት ይታያል። በራስህ ህይወትስ እግዚአብሄር ስራውን እንዴት እንደጀመረ ትዝ ይልሃል ወይ? የጀመረውን ከፍፃሜ ስለማድረሱስ ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ?

# ጥናት ሁለት (ፊሊ. 1፡1-11)

**የጥናቱ ዓላማ፡-** አማኞች አንዳቸው በሌላቸው ውስጥ በሚያዩት ነገር በመልካሙ በማበረታታት በሚጎድለው ደግሞ በመፀለይ ግንኙነታቸው እንዲዳብር ለማበረታታት።
**የጥናት መክፈቻ፡-** ሰዎች በህይወትህ ባሳየሀው መልካም ነገር አበረታተውህ ያውቃሉ ወይ? ያንን ማድረጋቸውስ ምን ያህል ጠቅሞሃል?

1. ፊሊ. 1፥1-11 በማንበብ ራስህን ከልድያ፥ ከእስር ቤቱ ዘበኛና ከአጋንንት ነፃ ከወጣችው ገረድ ጋራ አስቀምጠህ ይህንን ደብዳቤ ለመጀመሪያ ጊዜ ብታነብ የሚሰማህን ስሜት ግለጽ።
2. ከቁጥር 3-8 ባለው ክፍል ጳውሎስ ለፊሊጵስዩስ ሰዎች ያለውን ስሜት ምን ይመስላል?። ለምንስ የዚህ ዓይነት ስሜት የተፈጠረበት ይመስልሃል?
3. ጳውሎስ ስለፊሊጵስዩስ አማኞች እንደዚህ በእርግጠኛነት ሊናገር ያስቻለው ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ? (ቁ 6)
4. እግዚአብሄር መልካሙን ሥራ በራስህ ህይወትም ሆነ በቤተክርስትያንህ እየቀጠለና እያሳደገ ያለበት የምታየው መንገድ አለ ወይ?
5. ከቁጥር 3-8 ስለጤናማ መንፈሳዊ ግንኙነት ምን የሚያስተምረው ነገር አለ?
6. የፊሊጵስዩስ ሰዎች ከጳውሎስ ጋራ ያላቸውን አይነት የወንጌል ህብረት በህይወትህ ተለማምደህ ታውቃለህ ወይ? ይህንንስ አይነት ግንኙነት ለማሳደግ ምን ማድረግ ይረዳል ትላለህ?
7. ጳውሎስ ለፊሊጵስዩስ አማኞች የሚፀልየው ስለምንድነው? (ቁ 9-11)
8. እነኚህ የሚፀልይባቸው ርዕሶች እያንዳንዳቸው ለመንፈሳዊ ዕድገታቸው በምን መንገድ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ብለህ ታምናለህ?
9. በክርስትና ሕይወት ለማደግ በተለይም በከባድ ሁኔታ ሲታለፍ ሌላውን ማበረታታት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እነዚህን አማኞች ያበረታታሉ የምትላቸውን ሃሳቦች ከክፍሉ ውስጥ በመዘርዘር ተናገር። የፊሊጵስዩስ አማኞች አሁን ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ይህ የጳውሎስ ማበረታታት በምን መንገድ የሚረዳቸው ይመስልሃል?
10. ዛሬስ አንተ ሌሎችን በቃል፥ በፀሎት ወይም በሥራ ለማበረታታት እንደምትችል ታምናለህ ወይ? ታዲያ ወገኖችህን ለማነቃቃት ምን ያህል ትጠቀምበታለህ?

# ጥናት ሶስት (ፊሊ 1፡12-30)

**የጥናቱ ዓላማ፡-** አማኞች በህይወታቸው በአስቸጋሪና በአስከፊ ሁኔታዎች በሚያልፉበት ወቅት ከማጉረምረም የተሻለ መንገድ እንዳለና ይህም ጌታን በማስከበር ፈተናን ለመጋፈጥ ከጳውሎስ ህይወት እንዲማሩ ለመርዳት።

**የጥናት መክፈቻ፡-** በታሪክ ሰዎች ለተለያዩ ነገሮች እንደ ሃገራቸው፥ ቤተሰባቸው፥ ጓደኛቸው፥ አምላካቸውና ለመሳሰሉት ህይወታቸውን ሰጥተዋል። አንተስ ነፍስህን ልትሰጥለት የምትፈቅደው ነግር አለህ ወይ?

1. ፊሊ 1፥12-30 ያለውን ክፍል በማንበብ በጳውሎስ ላይ የደረሰ ተስፋ ሊያስቆርጥ የሚችል ምን ነገር ታያለህ?
2. ጳውሎስ ለምንድርነው በሚያልፍበት ሁኔታ ውስጥ ሲያጉረመርም የማይታየው? (ቁ 12-14)
3. በቁጥር 15-18 የሚገኙትን ሁለት ዓይነት ሰዎች አስተሳሰባቸውን አነፃጽር።
4. የሌሎች አስተሳሰብ(motive) የነቀፍክበት ጊዜ አለወይ? ይህንን በተመለከትስ ከጳውሎስ ምን ትምህርትን ትማራለህ? (ቁ 18)
5. በቁጥር 20-26 ውስጥ ጳውሎስ ሞትንና ህይወትን መምረጥ በተመለከተ የሚጠቅሳቸው ሃሳቦች ምን ምንድናቸው?
6. ጳውሎስ ለእኔ ህይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና(ቁ 21) ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል? የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ለአንተስ ለህይወትህ ሊኖርህ ስለሚገባህ አላማና አቅጣጫ ምን ያስተምርሃል?
7. ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ ሲል ምን ማለቱ ነው (ቁ 27-30)
8. እነዚህ በቁጥር 27-30 የተዘረዘሩት አመለከከቶችና ድርጊቶች ለምንድነው በተለይም በመከራና በስደት ውስጥ ሲታለፍ በጣም አስፈላጊ ሆነው የሚገኙት?
9. የሚከብዱ ሁኔታዎችን ለመቀበል የሚቻሉባቸውን ስንት ዓይነት አማራጮች ያሉ ይመስልሃል? ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ ጳውሎስ የትኛውን መንገድ ነው ሲጠቀም የሚታየው?
10. አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስትሆን በጳውሎስ ህይወት የምታየው ነገር ምን ያስተምርሃል? ከዚህስ አንጻር አመለካከትህን ለመቀየር ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት አራት (ፊሊ. 1፡1-18)

*የጥናቱ አላማ፡- የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትህትና የሞላበት አገልግሎት አማኝ ለክርስትና ህይወቱ መከተል የሚኖርበት ምሳሌ እንደሆነ ለማስገንዘብ።*

*የጥናት መክፈቻ፡- ኢየሱስ ዳግመኛ የማይመለስ ቢሆን አኗኗርህ ከአሁኑ በምን መንገድ የተለየ የሚሆን ይመስልሃል?*

1. ፊሊ. 2፥1-18 በማንበብ ሰዎችን ለማገልገል ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃደኝነት ከሆናቸው ወይም ከደረሱበት ነገሮች ሁሉ በአንተ አመለካከት በጣም ዝቅ ያደረገውና ያዋረደው የትኛው ይመስልሃል?
2. በቁጥር 1-4 ውስጥ ጳውሎስ ትህትናን በምን ዓይነት ነው የሚተረጉመው?
3. "ከእግዚአብሄር ጋራ መተካከልን መቀማት እንደሚገባ አልቆጠረውም" ብሎ ሲናገር ሃዋርያው ምን ማለቱ ነው? (ቁ 6)
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሄር ጋራ እኩልነቱን አለቅም ቢል ኖሮ ተልዕኮው በምን መንገድ የተለየ የሚሆን ይመስልሃል?
5. የራስህን ህይወት ስትመለከት በምን አቅጣጫ ነው የክብር መፈለግና የራስን ፍላጎት ብቻ የማርካት ፈተና የሚያስቸግርህ የሚመስልህ?
6. ክርስቶስ ያሳየውን ትህትና እግዚአብሄር እንዴት እንደተመለከተው ዘርዝር። (ቁ9-11)
7. ይህንን እግዚአብሄር ስለትህትና ያለውን አመለካከት ስታይ ስለአገልግሎት ያለህን አስተያየት በምን መንገድ ይቀይረዋል?
8. በቁጥር 12-13 ደህንነትህን እንድትፈፅምና በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር የደህንነቱን ሥራ በአንተ እንደሚሰራ ይናገራል። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሃሳቦች እንዴት ይታረቁልሃል?
9. እንዴት ነው በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል የተለየ ዓይነት ህይወት መኖር የሚኖርብን? (ቁ 14-16)
10. ቁጥር 16 ላይ "በአለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ።" ሲል ከላይ ካለው ሃሳብ ጋራ እንዴት የሚዛመድ ይመስልሃል?
11. "እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ" የሚለው በቁጥር 4 ላይ ያለውን ሃሳብ በቁጥር 17-18 ካለው ሃሳብ ጋራ በማነፃጸር በሃዋርያው ህይወት ይህ እውነት እንዴት የተገለጠ ይመስልሃል?
12. ከጌታ የተማርከውን የትህትና ምሳሌ በፊትህ ባሉት ቀናት መለማመድ የምትችልባቸውን ሁኔታዎችና መንገዶች ግለጽ።

# ጥናት አምስት (ፊሊ. 2፡19-30)

የጥናቱ ዓላማ፡- የጢሞቲዎስን፥ የአፍሮዲጡን፥ የጳውሎስንና እንዲሁም የፊሊጵስዩስ ክርስትያኖችን የሕይወት ምሳሌነት በመከተል አማኞች ለአገልግሎት እንዲነቃቁ ለማድረግ።

የጥናት መክፈቻ፡- የሕይወት ምሳሌነታቸው ለክርስትናህ እድገት አስተዋጽዖ ያደረጉ ሰዎችን ታስታውሳለህ? በምን ዓይነት እንደረዱህ ግለጽ።

1. ፊሊ. 2፥19-30 ባለው ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ሰዎች በሙሉ ዘርዝር?
2. የጢሞቲዎስን ህይወት ስትመለከት እንዴት ነው "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን" የሚለውን በተግባር ላይ እንዳዋለ የምታየው? (ቁ19-23)
3. በአሁን ዘመን የጢሞቲዎስ ዓይነት ሰዎች ለቤተክርስትያን ውስጥ መገኘት በምን መንገድ ይጠቅም ይመስልሃል?
4. አንተ ራስህን ስታይ የጢሞቲዎስን ፈለግ ተከትለህ ልታደርግ የምትችላቸው ምን ተጨባጭ ነገሮችን ይታዩሃል?
5. ጳውሎስ አፍሮዲጡን መልሶ ወደ ፊሊጵስዩስ የላከበት ምክንያት ለምንድነው?(ቁ 25-28)
6. በክርስቶስ፥ በጳውሎስ፥ በጢሞቲዎስና እንዲሁም በአፍሮዲጡ ውስጥ የጋራ የሆነ የህይወት ባህርይ የሚታይህ ምንድነው? (ቁ 25-30)
7. ለምንድነው እንደ አፍሮዲጡ ያሉትን ሰዎች እንድናከብር ሃዋርያው የሚመክረን? (ቁ 29)
8. በምን አይነት መንገድ ነው ለወንጌል የሚደክሙትን በግልም ሆነ በቤተክርስትያን ማክበር የምንችለው?
9. "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን" የሚለውን ሃሳብ እንዴት ነው የምትረዳው? ይህንንስ መረዳት በቀሪው የእድሜ ዘመንህ እንዴት በስራ ላይ ልታውለው እንደምትሞክር ለወገኖች ሃሳብህን አካፍል።

## ጥናት ስድስት (ፊሊ. 3፡1-11)

**የጥናቱ ዓላማ፡- ህግን በመጠበቅ የመጽደቅ ሙከራ ትርፉ ኪሳራ እንደሆነና የክርስቶስን ጽድቅ ተቀብሎ በምስጋና መመላለስ እውነተኛ የህይወት እረፍት መሆኑን ለመማር።**

**የጥናት መክፈቻ፡- መልካምና ፃድቅ ሰው እንደሆንክ ሰዎች ነግረውህ ያውቃሉ ወይ? ምን ዓይነት ስሜት በውስጥህ ተሰማህ?**

1. ፊሊ. 3፥1-11 ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ እያነጻጸረ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው?
2. ከቁጥር 4-6 ያለውን ክፍል በማንበብ አሮጌው ጳውሎስ ምን አይነት ሰው እንደነበረ ነው በራሱ ቋንቋ የሚነግረን?
3. ጳውሎስ አሮጌ ህይወትን በተመለከተ ለምን ይመስልሃል ጥብቅ የሆነ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው? (ቁ 2)
4. ቁ6 ላይ "በህግ ስለሚገኝ ጽድቅ..." ለእነርሱ መገረዝ ትልቅ ሥፍራ እንደተሰጠው በዘመናችንስ እንድንጠብቃቸው ግፊት የሚደረግብን ሰው ሰራሽ ህጎች ይኖራሉ ወይ? እስቲ ጥቂቶቹን ለመዘርዘር ሞክር።
5. እንደነዚህ ያሉት ወደ ህይወት የማያደርሱ ህጎች እንዴት ነው ክርስቶስን እንዳናውቅና በእርሱ እንዳንደሰት እንቅፋት ሊሆኑብን የሚችሉት?
6. ጳውሎስ የራሱን ጥሩነት ብቻ ሳይሆን የአንተንም ጭምር የሰውን ሁሉ ጥሩነት ለምንድነው እንደማይረባ የሚቆጥረው? (ቁ 8)
7. አዲሱ ጳውሎስ በምን መንገድ ነው ከአሮጌው ጳውሎስ የሚለየው? (ቁ7-11) የትምክህቱስ ምክንያቶች ከፊተኛው የሚለየው እንዴት ነው?
8. የጳውሎስ የህይወቱ ግቦች ምን ምንድናቸው? (ቁ 10-11)
9. በምን አይነት መንገድ ነው ሥቃይና ሞት ክርስቶስን በበለጠ እንድናውቀው የሚረዱን? (ቁ 10)
10. ጽድቅህ ክርስቶስ መሆኑን ምን ያህል ተረድተሃል? ይህስ መረዳት በክርስትና ህይወትህ ያመጣው ለውጥ ምንድነው? ወደፊትስ የህይወትህ ጉጉት ምንድነው?

# ጥናት ሰባት (ፊሊ. 3፡12-4፡1)

**የጥናቱ ዓላማ፡-** በክርስትና ህይወት የእድገታችን አንዱ ምልክት ሌሎች የደረሱበትን የህይወት ደረጃ ሳንንቅ በደረሱበት በደረጃቸው እንዲመላለሱ ነጻነት መስጠት እንደሆነ ለመማር፡፡
**የጥናት መክፈቻ፡-** ለአንድ ሳምንት በተከታታይ አንድ ሰው የምትገባባቸውንና የምትወጣባቸውን እንዲሁም የምታደርጋቸውን ነገሮች በሙሉ ቢከታተል በህይወትህ ከፍተኛ ሥፍራ የምትሰጠው ነገር ምን እንደሆነ መመስከር ይችላል ወይ?

1. በቁጥር 12-14 ውስጥ ጳውሎስ በመንፈሳዊ እድገት ስላለበትና እያደረገ ስላለባቸው ነገሮች የሚናገራቸውን ዘርዝር፡፡
2. 1ኛቆሮ 9፥24-27 እንዲሁም ፊሊ. 3፥12-16 የክርስትናን ህይወት በሩጫ ሲመስሉት ይታያል። ሩጫና የክርስትና ጉዞ የሚመሳለሉበትን መንገድ በማነጻጸር ተናገር።
3. እንደ ጥሩ ሯጭ ጳውሎስ ለራሱ የሚያደርገውና እኛም እንድናደርግ የሚመክረንን ምክሮች ከ1ኛቆሮ 9፥24-27 እና ከፊሊ. 3፥12-16 በማውጣት ዘርዝረህ ተናገር።
4. እጅህን ወደፊት መዘርጋትህን የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? እኛስ እጅን መዘርጋት ከሚልው አንጻር ልናደርግ የምንችላቸው ነገሮች ምን ነገሮች አሉ?
5. በሰልን የሚሉ አማኞች ሊኖራቸው ስለሚገባው የአመለካከት ዓይነት ጳውሎስ በቁ12-16 ውስጥ ይናገራል?
6. "በአንዳች ነገርም ልዩ ሃሳብ ቢኖራችሁ እግዚአብሄር ይህንን ደግሞ ይገልጥላችኋል" ከሚለው ጥቅስ ለሁላችን ሊጠቅም የሚችል ምን ሃሳብ ታያለህ?
7. በቁጥር 13-21 የክርስትያኖችንና የመስቀሉን ጠላቶች የዓላማና የግብ ልዩነት ያሳያል። ሐዋርያው ያሰፈራቸውን ልዩነቶች በማነጻጸር ተናገር።
8. ቁ 17 ትን ስታነብ አንድ አሰልጣኝ ቡድኑን ጠርቶ የእርሱን ምሳሌና ፈለግ እንዲከተሉ የሚነግር ይመስላል። አንተ እንድትከተላቸው ጸሐፊው የሚፈልጋቸው እውነቶች ምን ይመስሉሃል?
9. በሃሳብህ የማይስማሙህን ወገኖች የምታስተናግድበት መንገድ ምን ይመስላል? እንደ ቁ15 መሰረት ምን የሚጠበቅብ ይመስልሃል? ሌሎች ያለህበትን የእድገት ደረጃ ሊቀበሉልህ እንደምትወድ አንተም ሌሎችን ባሉበት ለመቀበል ልብህን አስፋ፡፡

# ጥናት ስምንት (ፊሊ. 4፡2-9)

የጥናቱ ዓላማ፡- በግል ህይወታችንና በቤተክርስትያናችን የሚያስጨንቁንን ነገሮች ለይተን ለማወቅና እግዚአብሄርን መተማመን እንድንማር።

የጥናት መክፈቻ፡- ውጥረት(stress) የሚለውን ሃሳብ አገር ቤት ሳለህ ሰምተህው ወይም ተለማምደህው ታውቅ ነበረ ወይ? አሁንስ በዚህ ባለንበት አገር?

1. ፊሊ. 4፥2-9 በማንበብ በፊሊጵስዩስ ቤተክርስትያን ሊያስጨንቁ የሚችሉ ምን ነገሮች ታያለህ? በአጠቃላይስ ሰዎችን ሊያስጨንቁ የሚችሉ ጥቂት ነገሮችን ዘርዝር?
2. በቁ 2 ላይ ኢዮዲያንና ሲንጤኬንን እንዲስማሙ ሲመክር ይታያል። የእነርሱ ግንኙነት መደፍረስ በቤተክርስትያኒቱ መንፈሳዊ ጤንነት ላይ ሊያስከትል ይችላል የምትለውን ነገር ተናገር፡፡
3. እነዚህን ሁለት ግንኙነታቸው የሻከረን ሰዎች ጳውሎስ አብረህ የተጠመድህ ብሎ የሚጠራው ሰው በምን ዓይነት ነው እንዲረዳቸው የተጠየቀው?
4. በወገኖች መሃል ወይም በቤተ ክርስትያን ለሚፈጠር አለመግባባት በዚህ ክፍል መሰረት አንተ ምን ማድረግ የምትችል ይመስልሃል?
5. በጌታ ደስ መሰኘት በህይወት የሚመጡትን ውጥረቶች(stresses) በምን ዓይነት ጎገድ የማርገብ ችሎታ ያለው ይመስልሃል? (ቁ 4)
6. ጸሎት በህይወታችን ሊኖረው የሚገባው ስፍራ ምንድነው? (ቁ 6-7)
7. ጸሎት ሊያስገኘው ስለሚችለው ውጤት ጳውሎስ የሚናገረው ምንድነው?
8. በቁጥር 8 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ከላይ በቁ 4-7 ከተጠቀሱት ነገሮች(በተለይም ከአዕምሮ ሰላም) ጋራ ሊኖራቸው የሚችለውን ግንኙነት አስረዳ።
9. ከራስህ ልምድ ብዙ ጊዜ ሃሳብህን ለመሰብሰብና ለመረጋጋት የተጠቀምህባቸው መንገዶች ካሉ አካፍል?
10. በቁጥር 9 ላይ ጳውሎስ የተማርነውን በስራ ላይ ስናውለው የሰላም አምላክ ከእኛ ጋራ እንደሚሆን ያረጋግጥልናል። ከዚህ ክፍል የተማርከውና በህይወትህ በስራ ላይ ልታውለው የምታስበው አንድ ነገር ምንድነው?

# ጥናት ዘጠኝ (ፊሊ. 4፡10-23)

የጥናቱ ዓላማ፥- ለወንጌል አገልግሎት መስጠት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ለማስተማርና ቅዱሳንን የዚህ በረከት ተካፋዮች እንዲሆኑ ማበረታታት።
የጥናት መክፈቻ፥- ለእግዚአብሄር ስራ የምታውለው በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ቢኖርህ በምን አገልግሎት ላይ ታውለዋለህ? ለምን ይህንን ከሌላው ከፍ አድርገህ አየህው?

1. ፊሊ. 4፥10-23 በማንበብ ከፊሊጵስዩስ ሰዎች ስጦታ በጣም ያስደሰተው ነገር ምንድነው ትላለህ?
2. ሐዋርያው ለምንድነው በእነርሱ ስጦታ ላይ እንደማይደገፍ ግልጽ ሊያደርግላቸው የሚሞክረው? (ቁ 11-13)
3. ጳውሎስ እየኖረበት ያለውን የመርካትን ምስጢር ያገኘበት መንገዱ ምን እንደሆነ ነው የሚነግረን?
4. ሰዎች ስንባል ባለን ነገር ለመርካት የምንቸገረው ለምን ይመስልሃል? ታዲያ ጳውሎስ የሚናገረውን ዓይነት ርካታ እንዴት መለማመድ ይችላል ትላለህ?
5. የፊሊጵስዩስ ክርስትያኖች ከጳውሎስ ጋራ ወንጌልን በመስበክ ተባብረዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? ይህንን ይልክበትን ምክንያት አስረዳ። (ቁ 14-18)
6. የፊሊጵስዩስ አማኞችን ለእግዚአብሄር ሥራ አሰጣጥ ከራስህ ልግስና ጋራ ስታነጻጽር ምን የምትማረው ነገር አለ?
7. የፊሊጵስዩስ አማኞች ለእግዚአብሄር ሥራ በልግስና ስለሰጡት ስጦታ ጳውሎስ ከጌታ እንደሚቀበሉ የሚያምነው ምንድነው? (ቁ 17-19)
8. በቁጥር 19 ላይ የምንመለከተው ቃል ኪዳን ለጌታ ሥራ እንድንሰጥ በምን መንገድ ያበረታታናል?
9. ለእግዚአብሄር ሥራ በማለት በዚህ ዘመን ብዙ አገልጋዬች ገንዘብ ይጠይቃሉ። በዚህ ባጠናነው ክፍል ውስጥ ሰጪውንም ሆነ ተቀባዩን አስመልክቶ የምትማረው ምን መመሪያ አግኝተሃል?
10. ይህ ያጠናኸው ክፍል ለእግዚአሄር ሥራ ስለመስጠት ያለህን አመለካከት ለመለወጥ ረድቶሃል ወይ? እንዴት?

# ጥናት አስር (ፊሊጵስዩስ ማጠቃለያ)

***የጥናቱ ዓላማ፡- የመጽሃፉን አጠቃላይ ሃሳብ ለመረዳትና ዋና ዋና ሃሳቦችን በህይወታችን ለመቅረጽ ነው።***

***የጥናት መክፈቻ፡- ከመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መጽሃፍ በመምረጥ በግልህ በጥልቀት ያጠናህበት ጊዜ አለ ወይ? ዛሬ አንድ መጽሃፍ መጨረስ ስላስቻለን ጌታን እናመስግን።***

1. **ፊሊ 1፥21 የምዕራፍ አንድን ሃሳብ በጥቅል የያዘ እንደሆነ ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይስማማሉ። አንተስ በዚህ ሃሳብ ትስማማለህ ወይ? ለምን ይህንን እንዳልክ አስረዳ።**
2. **ፊሊ 2፥5 ለአንተ የሚሰጥህ ትርጉም ምንድነው? የክርስቶስ አዕምሮ አለን ሊያሰኙን የሚችሉትን ጥቂት ነገሮች ዘርዝር።**
3. **ፊሊ 2፥1-11 ያለውን ክፍል አንብበህ ስለራስህና ስለሌሎች ሊኖርህ ስለሚገባ አመለካከት ምን እንደሚያስተምርህ ተናገር።**
4. **በፊሊ ምዕራፍ 3 ለሰፈረው ሃሳብ ዋነኛ ሃሳብ በ3፥8 ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ይህ ጥቅስ ለማንኛውም አማኝ ያስተላልፋል የምትለው እውነት ምንድነው?**
5. **ፊል 3፥12-21 ባለው ክፍል የምታያቸውን ሁለት ዓይነት ሰዎች ዘርዝር። በእነዚህ ሰዎች መሃል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት አነጻጽር።**
6. **በፊሊ 4፥13 በማንበብ ያለኝ ይበቃኛል የሚለውን ትምህርት በተማረና ባልተማረ አማኝ ምሃል ሊታዩ የሚችሉትን ጉልህ የሆኑ ልዩነቶች ዘርዝር።**
7. **ፊሊ 4፥10-22 ስናነብ መስጠትን በተመለከተ ብዙ ነገሮችን እናገኛለን። ከዚህ ሁሉ ጎላ ብሎ ለአንተ የሚታይህ ሃሳብ የትኛው እንደሆነ ተናገር።**
8. **የፊሊጵስዩስን መጽሃፍ በማጥናትህ ምክንያት በህይወትህ ጌታ እንደረዳህ ልታደርግ ያቀድከው ለውጥ ካለ ለወገኖች አካፍል።**